# ሰጥቶ መቀበል

መተካት ከቻልን ፤ መለሰን በስዬ
ገብሩን እንስጥና ፤ ይምጣ . . አቦይ ጸሀዬ
ሥዩም መስፍን መጥቶ ፤ በርሄ ቢከተል
አረጋሽን ሰደን ፤ አዜብን መቀበል
ወደኛ ከመጣ ፤ በረከት ስምዖን
እንለውጣቸው ፤ በመንግሥቱም ቢሆን
ይቀየር ካላችሁ ፤ ብአዴኑ ህላዊ
የጎጠኞች ንጉሥ ፤ ይሂድ አረጋዊ
ስብሀት ነጋንም ፤ ወይም አባዱላ
ያስቀየመ ካለ ፤ በቅርስ የተጣላ
የቀድሞ ወያኔ ፤ አዳሪ የሚጉላላ
ቦታውን ይያዘው ፤ በየስፍራው ይሙላ ።

እነሱም ሳይነኩን ፤ እኛም ሳንነካ
ሰው . . ታሪኩን ሳናይ ፤ አረካ አላረካ
በሰጥቶ መቀበል ፤ ስልጡን ፖለቲካ
የቀድሞን ወያኔ ፤ ባዲሱ እንተካ ።

በዘዴ . . ነው እንጂ ፤ ወያኔን ማባበል
አክራሪዎች ሆነን ፤ አጉል ስንታገል
እንዳይበሳጩ ፤ በምርጫው መቀጠል
ስልጡን ፖለቲካ ፤ ሰጥቶ ነው . . መቀበል ።

ሰጥቶ መቀበሉን ፤ ካረጉት መሸወድ
ትግላችን ከሆነ ፤ ሰዶ ለማሳደድ
እግዜር ይይላቸው ፤ መድህኒያለም ይፍረድ
ዳግመኛ ወያኔ ፤ አይሆነንም ዘመድ ።

ታዛቢው ... March, 16, 2010